<u>ድንቄም ሰፊ ግንባር!!--የወያኔ ትሎች ሲርመሰመሱ</u>

ተድላ ሙሉጌታ

" እነርሱም በጨለማ መንገድ ይሄዱ ዘንድ
የቀናውን ጎዳና የሚተው
ክፉ በመሥራት ደስ የሚላቸው
በጠማማነት ደስታን የሚያደርጉ
መንገዳቸውንም የሚጠመዝዙ
አካሄዳቸውንም የሚያጣምሙ ናቸው::"

(መፅሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 2)

አውቆ የተኛን ሰው የሚቀሰቅሰው አይኖርም እንደተባለው ዕድሜም ተመክሮም ሳያንሳቸው አውቀው በጠማማ ጎዳና የሚጓዙትን አተፊዎችና ከሀዲዎች ማለት ተገቢ ነው:: ሰሞኑን የአንጃዎቹ መሪ ከበራዳ ስዊድን ወደ በራዳ አሜሪካ መንገዱን አቅንቶ የለመደበትን ጠማማነት በሌሎች ላይ ሊያጋባ እየደዋወለ ነው:: በአዲስ አበባ ያሉት ክፉ መስራት ደስ የሚላቸው ደግሞ መድረክ ያሉት ላይበቃ ተባብረናል፣ በአንድነት ለምርጫ ልንቀርብ ተዘጋጅተናል ሲሉ በቃሊቲ ያለችው የወይዘሮ ብርቱካን ቡድን ደግሞ ተደባልቂያለሁ ብሎ መንገዱን በይፋ ጠምዝዟል:: በዚሁ መድረክ ለመጠቃላል አንጃውም ማመልከቻ አስገብቷልም ቢባልም እነ ገብሩ ይህን ያህል ጉጉት አላሳዩም እየተባለ ነው::

ባለፈው ስለ ሰፊ ግንባር የፃፍኩትን በተመለከተ ያገኘሁት ማብራሪያ ወይም ምላሽ የለም:: ዶክተር ብርሃኑ ወደ ሲያትል (አሜሪካ) ዘልቆ በ "ጋሻው" ድረ ገፅ የወጣውን የጋራ መግለጫ አላየሁም አላውቀውም ብሎ ክዷል:: ታዲያ አንጃውስ ለምን ይህን የጋራ ስምምነት ሲያዳንቅ ከርሞ ከደፈረ መግለጫውን በድረ ገፁ አላወጣውም? እውነቱ ግን ስምምነት መደረጉ ነው:: አንጃው፣ ግንቦት 7፣ ኢሕጉ ፣መኢሶን፣ታንድ የአቶ አረጋዊ፣ ህብረ ሕዝብ የመቶ አለቃ አያልሰው (አዲሱ ስማቸውን ዘነጋሁት)፣ የወይዘሮ ብርቱካን ድጋፍ ኮሚቴዎች ናቸው ተስማማን ያሉት:: በ ጋሻው ድረ ገፀ ያለው ይህ ነው:: ዶክተር ብርሃኑ ዓይኔን ግንባር ያርገው አላየሁትም ቢልም ይህ የህብረት ንግግር በነዚሁ መቀጠሉ ደግሞ የአደባባይ ምስጢር ነው:: አንጃው በተለይ ሰፊ ህብረት መሰረትኩ ለማለትና ከወያኔ ጫማ ስር ለመውደቅ እየቸኮለ መሆኑ ተነግሮለታል:: ለዚህም ነው በስንት ጀግኖች ኮከቦቿ በቀላው " ዴሞክራሲያ" ስም አልፎ አልፎ አምጠው በሚያወጡት ዝቃጭ ፅሁፋቸው የቀድሞ ጓዶቻቸውን ገዳዮችና አሳሪዎች እነ ገብሩ አሥራትን አዳንቀው የፃፉት:: ዶክተር ብርሃኑ በአጭር ጊዜ (ከዓመት ተኩል እስከ አምስት ዓመት ባለ ጊዜ ገደብ) ወያኔን አፈር እናበላዋለን ገንዘብ አዋጡ እንጂ ሲል የተሰማ ሲሆን ከመቼው ትጥቅ ትግሉ ተረስቶ የተከበርክ ወያኔ ሆይ በሩን ገርበብ አድርግልና ምርጫ እንግባ ልመናውን ጀመረ?

አንጃው እንኳን ከድርጅት የፈለሰው ወደ ወያኔ ካልገባሁ ፤አፈዳቪት ፈርሜና ታማኝነቴን አረጋ ግጬ፤ በድርጅቱና በሰማዕት ላይ ተፍቼ ልወይን በማለይ ስለሆነ በተለይ አዛውንቱ የአንጃ መሪ ቅሌት ብቻ ተሸክሞ በስደት መና እንዳይቀር ቶሎ እንግባ ብሎ መራወጡ አያስገርምም። ሰፊ ግንባር የሚባለውን ለሁሉም ስም መደበቂያ ነው፤ መልክ--ምግባረ ጥፉነታቸውን ብቻ ሳይሆን ለወያኔ እንዲያመች ነው። የመለስ ቡድን ሰማይና መሬት ቢጋጠሙ መኢሶን የተባለ ቡድን በተለ ይም በዶክተር ነገደ መሪነት ህጋዊነትን አያገኝም ባይ ነው። እስካሁን ያልተቀየረ ሌላ አቅዋሙ ደግሞ ኢሕአፓ አንጃ ወይም (አትሳቁና) ዴሞክራት ቢባልም ያን የሚጠላውን ዋና ስምን ኢሕአ ፓ የሚለውን የያዘ ነውና ይህ ስም መቸም ቢሆን በምንም ዓይነት ህጋዊ ሆኖ በእኔ አይጠራም የሚል ነው። ሰለዚህ ሁሉን አቀፍ የሽፋን ስም ያስፈልጋል። አሊያማ (ግንቦት 7 ከሌለ) አንጃና ነገደና አረጋዊና መቶ አለቃና ኢሐን ተደምረው ሁለት አስር በላይ መሆናቸው አነጋጋሪ ነው። ለዚህም ነው አይታክቴው የአንጃው አዛውንት ለዓመታት ያቃተውን ዳግም በቀቢፀ ተስፋ ለመሞከር ወደ አሜሪካ እንደገና ዘልቆ " የቀድሞዎች" የሚላቸውን በልመና ለማቀፍ ጎተት ጎተት የሚለው። ፍሬ አልባ ልፋት። ትላንት ኢዴኃጎ ተብሎ በዚህ ውስጥ ትንሽ ሻል ያለ ሚዛን የነበራቸውና ከኢሕአፓ ጋር ገጥመው የነበሩት የበየነና መረራ ቡድኖች ያው ትግል ለምኔ ፓርላ ማ ነፍሴ ብለው ከከዱ በኋላና ኢሕአፓም ከዚሁ ከቀሪው ቀፎ ራሱን ካገለለ ወዲያ ኅብረት የተባለው መሞት መቀበሩ ምስጢር አይደለም። ይህን ሬሳ አሁን ከግንቦት 7 በማስተቃቀሡፍና ብሎም ከገብሩ አስራት መድረክ ለማያያዝ በመሞከር ነፍስ ሊዘሩበት እየጣሩ ነው። ከሬሳ ጋር አልተቃቀፍም ያለው ዶክተር ብርሃኑ ለምን ሀሳቡን እንደለወጠ ባይታወቀም ሰውየውን ያቀሰሰ ው ጠባዩ ክህደትና መወላወል ነውና አያስደንቅም ብሎ ማለፍ ይቻላል።

" ከዕቡያን ጋር ምርኮ ከመካፈል
ከትሑታን ጋር በተዋረደ መንፈስ መሆን ይሻላል።" (መፅሐፈ ምሳሌ)

ሕዝብን ከድተው ከወያኔ ስር ለመሰለፍና የወያኔ ትሎች ለመሆን ራሳቸውን ያጬትና ያዋረዱት አንጃዎች በአሁኑ ጊዜ ዕፁብ ድንቅ ብለው እያደነቁት ያሉት የስዬ አብርሃና ገብሩ አሥራት ቡድን በኢትዮጵያ ላይ ወያኔያዊ ወንጀልን ሲፈፅም የቆየ መሆኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ የለም። የመድረኩ ስብስብ ሊቀመንበር ተብሎ የተሾመው ገብሩ አስራት የወያኔ ድርጅት ዋና መሪዎች አንዱ ሆኖ በወገኖቻችን ደም የታጠበ ነው። የትግራይ ገዢ ተብሎ ሳለም እስር ቤቶችን በንፁሀ ን የሞላ፤ ነፃ ጋዜጦች ትግራይ አይገቡም ብሎ የከለከለ ፤ሻዕቢያን አትንኩ ብሎ ስንት የትግራይን ተወላጅ ያጠፋ ወንጀለኛ ነው። ገብሩ አሥራትም ሆነ ስዬ፤ ከጀርባ ያሉት መሰሪዎች አለምሰገ ድና ተወልደ (ስለነዚህ ወያኔዎች የተስፋየረ ገብረአብን መፅሀፍ ያነቧል) የጎንደርና ወሎ ለም **መሬት በወያኔ ወደ ትግራይ መጠቃለሉን የደገፉና ዛሬም ቢሆን በተፃራሪው ትንፍሽ ያላሉ ናቸው።** በግንጠላውም ሂደት--ዛሬ አሰብ ይመለስልን ብለው ሊያደናግሩ ቢሞክሩም-- ከመለስ እኩል ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተው **ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ያደረጉ ከህዲዎች ናቸው።** ከነዚህ ወያኔዎች (በነገራችን ላይ አሁንም ቡድናቸው አረና

ጠባብ ብሄረተኛ የትግራይ ቡድን ነው) ጋር በመድረክ የተቃፉትንም ስናይ አፍንጫችንን መዝጋ ት እንገደዳለን:: የመለስ መጋዣ ሆኖ በፕሬዚዳንነት ሲዋረድ የቆየው "አይጠቅም-- አይጎዳ" ነጋሶ ጊዳዳ (አማርኛ ስናገር ያመኛል ሲለን የነበረው)፣ ሕዝብን በተከታታይ የካደውና የሙት ከተማ አድማን በማጨናገፍ ወንጀል የፈፀመው ና ፍርዱን የሚጠብቅው በየነ ጴጥሮስ፣ ፖለቲካ ለጡረታ ባዮ ሽማግሌ ቡልቻ ደመቅሳ ናቸው:: ጥርቅሙ ቀደም ሲል ሕዝብን የከዳ አሁንም ሕዝብን የከዳ ነው:: ከዚህ ጎራ ነው አንጃዎቹና የቀድሞ ጎብረቶች ሊገቡ ሚንፏቀቁት ማለት ነው:: የነገብሩ አሥራት ስምሪት የትግራይን ማለትም ለነሱ የወያኔን የበላይነትን ማስቀጠል ነው: : ብፃያቸው መለስ ቅንጅትን ሲያፍንና ሕዝብን ሲፈጀ በሚገባ ለማውገዝ አቅቷቸው እንደቆየ አይተናል:: የወያኔን የረጅም ዓመታት ወንጀልና ምስጢር አንድም ቀን አላጋለጡም:: ገብሩ አሥራት ወደ አሜሪካ መጥቶ ለትግራይ ተወላጆች ብቻ ስብሰባዎቸ ሲያደርግ በሆነ ቦታ ስለነ ፀጋዬ ደብተራው መታሰር ሲጠየቅ ከመካዱ ሌላ ኮለኔል ቃለ ክርስቶስ አባይም በወያኔ እስር ቤት የሉም ብሎ ክዶ ነበር:: ገብሩ ከካደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መለስ ኮለኔሉን ለቋቸው መፅሀፍም ፅፈው ህይወታቸው አልፏል:: ታዲያ ከመለስ የባሱ እንጂ የተለዩ ያልሆኑት እነ ገብሩና ስዬ ናቸው የሚደነቁና የሕዝብ ትግል አሰባሳቢ የሚባሉት? የኢሕአፓ አንጃ የሰው ባዶ፣የወያኔ ትል ቢባል ይበዛበታል? ወደ ወንጀል ስንመጣ በተለይ ከገብሩ እስከ ስዬ የወያኔን ወንጀል ማለትም ወንጀላ ቸውን በተመለከተ የተነፈሱት የለም:: የመለስ ምስጢር ምስጢራችን ብለው ደብቀዋል:: ስዬ ከሚቹ ኃየሎም ጋር ሆኖ የጃተኔ አሊን መገደል ወስኖ ወደ ናይሮቢ ገዳዮች ልከው ገድለውታል:: አፈወርቅ ዓለም ሰገድም (የወያኔው መሪ የሙሉገታ ወንድም) በቲካ ስደተኛ ሰፈር በስዬና ክንፈ ገብረ መድህን በተላኩ ነፍስ ገዳዮቸ ተገድሏል:: አሰፋ ማሩና ተስፋዬ ታደሰም በአዲስ አበባ ተገድለዋል:: ፕሮፌሰር አሥራትም ለሞት ተዳርገዋል:: ታምራት ላይኔም ላይ ሴራውን ጎንጓኝና አስፈራሪ ስዬ ራሱ ነበር:: ሰለነዚህና ሌሎችም ስዬም ገብሩም ሌሎቹም ትንፍሽ ያሉት የለም:: ከሙስናው ባሻገርና ወጣት ሴቶችን በመድፈር ስዬ የተከሰሰውን ሳናነሳ:: ድንቂም ነፃ አውጪ! ድንቂም ሰፊ ግንባር መሪ!!

የወያኔ ትሎች ወያኔ ከጣለው እበት የተፈጠሩ ናቸው:: ስዬና ገብሩ ዓይነቶቹ የዛሬን አያርገውና ትላንት ፈላጭ ቆራጭ ወያኔዎች ነበሩ:: የወደፊት ምኞታቸውም ጠባብ ዘረኛ የበላይነታቸውን ለማቆየት ነው:: አንጃው ግን ተራ ቆሻሻ ትል ነው:: ከሀዲና እበላ ባይ:: በሩዉ ሳይሆን በቅርቡ በሕዝብ ዘንድ ዋጋቸውን የሚቀበሉና የሚዋረዱ መሆናቸውም አያጠራጥርም:: አንጃውንና መሰል ከሀዲዎችን ተከትሎ ወደ ወያኔ ጫማ ስር ሊረገጥ ሊዋረድ መሄድ የተዘጋጀው ሁሉ ቤት መሬት እመራለሁ፣ አሾማለሁ ከሚለው ቅዠት አልፈው የፍርድ ቃጭልና የሕዝብ የበቀል ጩኸት ሲያስተጋባ መስማት ይቻላቸው ዘንድ እንፀልይላቸዋለን:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ባይሆ ን ነገ ተነገ ወዲያ ሂሳብ ያወራርዳል፣አልፎም ይህ እርምጃ የከፋም ሊሆን ይችላል:: የተቀለደበት ሕዝብ በቀለዱበት ላይ ሲነሳና ምድር ቀውጢ ስትሆን ዋ ሕዝብን ላሳዘኑና ላስለቀሱ ሁሉ !! ሕዝብን መካድ ጥፋት፣ወንጀል፣ ኃጢያት ነው:: ሰውም እንደ እጁ ሥራ ዋጋውን መቀበሉ መቸም አይቀርምና የወያኔ ትሎችን ማሯቸው የሚልላችሁ አታገኙም::